# የACPS Express 3/4/2022: የ'State of the Schools' - ማጠቃለያ

## የ'State of the Schools' - ማጠቃለያ




የአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)፤ በACPS 2025 Equity For All Strategic Plan እና በ2021-22 Areas of Focus ግቦችን ያሟሉ የትምህርት ቤት ክፍሎችን ላይ አዲስና ማሻሻያዎችን (updates) ካጋሩን - ከጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ፣ ዶ/ር ግሪጎሪ ሲ. ሃችሂንግስ (Dr. Gregory C. Hutchings, Jr) ጋር፣ የመጀመሪያ ዓመታዊ የ'State of the Schools' ዝግጅትን - በማርች (March) 1 ቀን 2022 አዘጋጅቷል። ተማሪዎች፣ ሠራተኞች፣ ተመራጭ-ሹሞች እና የክፍል አመራሮች፤ ከአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School) - በዚያኑ-ጊዜ (simultaneous) ትርጉም በስፓኒሽ፣ አማርኛ እና አረብኛ የሚተረጉሙ ጋር - ዝግጅቱን በቀጥታ-ሲያሰራጭ፤ የማህበረሰብ አባላቶች እና አጋር ድርጅቶች አብረው ተካፍለዋል።

"ቡድናችን፤ የ'2025 ACPS Strategic Plan: Equity for All' ላይ ያለንን ግቦች ለማሟላት ጠንክረው የሚሰሩ፣ እና አሁንም-ገና ብዙ የሚሰራ ነገር እንዳለ ሳንረሳ - እስካሁን ባደረግነው የእድገት-ሂደት ደስተኞች ነን፤" ብለዋል ዶ/ር ሃችሂንግስ (Dr. Hutchings)። "ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ - ሠራተኞቻችን እና ተማሪዎቻችን የሚደነቅ-አልበገር ባይነትን ያሳዩ፣ እንዲሁም ቤተሰቦቻችንን፣ የትምህርት ቤት ቦርድ፣ እና የአሌክሳንድርያ ከተማ አመራርን - ለተማሪዎቻችን ትምህርት እና የወደፊት ሕይወት ጥቅም-እንዲያገኙ፣ አብረው-በትብብር መስራታቸውን፤ ላመሰግን እወዳለሁ።" ዶ/ር ሃችሂንግስ (Dr. Hutchings)፤ ለስልታዊ ዕቅድ (Strategic Plan) ስኬታማነት - እንዴት የ'Equity Dashboard' እና የ'Equity Climate' የዳሰሳ-ጥናትን ማስጀመር ወሳኝ-ነገር እንደሆነ አስምረውበታል። ስልታዊ ዕቅዳችን (Strategic Plan) ስኬታማ እንዲሆን፣ መንገድ-እንዳንስት አድርጎ የሚያቆየን ይዘቶችን ያለው ተጠያቂነትን እና የምንሰራውን ስራ እና የምናሳየውን የእድገት-ሂደት ሁሉም እንዲቆጣጠሩን ግልጽነትን መገንባት እንዳለብን እናውቃለን፤" በማለት ገልጸዋል፣ ዶ/ር ሃችሂንግስ (Dr. Hutchings)።

ያቀረቡትን-ገለፃ (presentation) ተከትሎ፤ ከዌቢናሩ (webinar) በፊት ከተማሪዎች፣ ሠራተኞች እና ቤተሰቦች - የገቡትን ጥያቄዎች - እንዲሁም፣ ዝግጅቱን በአካል (in person) የከተካፈሉ ተማሪዎች የቀረቡትንም ጥያቄዎች፤ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጁ መልስ ሰጥተውበታል። ጥያቄዎቹ ያካተቱት፤ እንደ የ'Social Emotional Academic Learning (SEAL)'፣ ያለማቋረት በመቅረት ላይ (curb truancy) ስልቶችን በመፍጠር ላይ፣ በACPS ትምህርት ቤቶች እና የክፍሉ አጋሮች ከሆኑ - እንደ ቨርጅኒያ ቴክ (Virginia Tech) እና አማዞን (Amazon) ካሉት ጋር ፍትሃዊ-እኩልነት (equity)፤ በሚሉ ርዕሶች ላይ ያካተተ ነበር።

የዌቢናሩ (webinar) የተቀዳው-ቀረፃ፣ በACPS ድህረ-ገጽ ላይ፣ ከዶ/ር ሃችሂንግስ (Dr. Hutchings) ለዚህ ዝግጅት ካቀረቡት-ስላድ (slide presentation) ጋር፣ እና የ2020-21 የትምህርት ዓመት አዲስ ሪፖርት ከሆነው፤ "Measuring What Matters" ጋር፣ የሚገኝ ይሆናል።

## የሴቶች ታሪክ (Women’s History) ወር - የማንነት መግለጫ (Profile): ናኦሚ ኤል. ብሩክስ (Naomi L. Brooks)



በኤፕሪል (April) 14 ቀን 1934 ዓ.ም የተወለዱት - ናኦሚ ልዊስ ብሩክስ (Naomi Lewis Brooks)፤ በ“seminary mudtown” በጣም ትሁት ከሆነ አጀማመር እስከ የ85 ዓመት-ዕድሜ ያለው ‘dynamic matriarch’ የሆነው - የከተማው ታዋቂ ቤተሰቦች፤ ዕውነተኛ-ማራኪ የሆነ ሕይወትን እንደ “ተፈጥሮአዊ (The Natural)” በመሆን መርተዋል።

ባለቀለም-ለሆኑ ልጆች (Colored Children) ትምህርት ቤት በሆነው በሴሚናሪ (Seminary) ትምህርት ቤት ውስጥ - በአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School) አሁን በቆመበት ውስጥ ከተማሩ በኋላ፤ ወደ ላየልስ-ክራውች (Lyles-Crouch) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ፓርከር-ግሬ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Parker-Gray High School (PGHS) በከተማ-አውቶቡስ ተጉዘዋል። ብሩክስ (Brooks)፣ በዘር-ከሚከፋፍል ሁሉም-ጥቁር የሆነው ‘PGHS’፣ በ1951 ዓ.ም፤ ከክፍላቸው ሁለተኛ ሆነው ተመርቀው ነበር። ከ‘PGHS’፣ በላቀ-ድረጃ (honors) መመረቃቸው እና ጠንካራ ተማሪ መሆናቸው ብቻ ሣይሆን፣ ኮከብ አትሌትም ነበሩ። በሴቶች የባስኬት-ቦል (basketbal) ቡድን ውስጥ የፊት-አጥቂ የነበሩ እና፣ ብዙ ነጥቦችን በሲዝኑ (season) ውስጥ - በአንድ-ነጠላ ጨዋታ ውስጥ ብዙ ነጥቦችን በማስመዝገብ የትምህርት ቤት ሪከርድን አግኝተው ነበር።

ከከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኋላ፣ ሚስ ልዊስ ብሩክስ (Ms. Lewis Brooks)፤ የባችለር ሣይንስን በመጀመሪያ-ደረጃ ትምህርት፣ ከቨርጅኒያ ስቴት ኮሌጅ (አሁን የቨርጅኒያ ስቴት ዩኒቨርስቲ-ከሆነው) በማግኘት፤ እንደ-ትምህርት-ሰጪ ሆነው እራሳቸውን በሰንጠረዥ አስቀምጠዋል። በቻርልስ ሂውስተን (Charles Houston) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በ1955 ዓ.ም የማስተማር የስራ-ድርሻን የተቀበሉ እና፣ ከቨርጅኒያ ስቴት ዩኒቨርስቲ፣ በመጀመሪያ ደረታ ትምህርት - የ‘M.E.’ን ለማግኘት ይሄዱ ነበር። ከዚያ-ቀጥሎ በኮራ ኬሊ (Cora Kelly) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ፣ አስተምረዋል። በመጀመሪያ ደረጃ እና በአዋቂ ትምህርት - የስራ መስካቸው ላይ አጠንጥኖ የሚገኘው በ25 ዓመታት ጊዜ ዙሪያ ነው።

ብሩክስ (Brooks) ሁልጊዜ፤ “በተተከለበት ቦታ ሁሉ የሚያብብ” በመሆን፤ በወታደራዊ ቤተሰብ ምንክያት በተደጋጋሚ ከቦታ-ወደቦታ የሚዘዋወሩ፣ እና በየሄዱባቸው አካባቢዎች፣ የራሳቸውን ልጆች፣ ተማሪዎችን እና ወታደሮችንም ሳይቀር በማስተማር ለውጥ-የሚያመጡ ነበሩ።

በሜይ (May) 21 ቀን 2020፤ ሚስት፣ እናት፣ ትምህርት-ሰጪ እና መሪ፤ የነበሩት በሞት ተለይተዋል። የሕይወት-ጉዞአቸው በመጀመረበት እና በአበቃበት - በአሌክሳንድርያ ውስጥ በሚገኙ ባስተማሯቸው በሁሉም ሰዎች ውስጥ ሆኖ፣ ቅርሳቸው በሕይወት

እየኖረ የሚቀጥል-ይሆናል። እንደ ‘Identity Project’ አንዱ-አካል በመሆን፤ የ‘ማቲው ሞሬ (Matthew Maury) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት’፣ ወደ ናኦሚ ኤል. ብሩክስ (Naomi L. Brooks) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት - ተብሎ በጁላይ (July) 1 ቀን 2021 ላይ ስያሜውን አግኝቶ ነበር። ለተጨማሪ መረጃ፣ በኦንላይ - በ The Identity Project ላይ ይገኛል፡፡

## ብሄራዊ የትምህርት ቤት የማህበራዊ ሠራተኛ (Social Work) ሣምንት: ከማርች (March) 6- 12



ከማርች (March) 6-12 ቀን ለሆነው - ለ‘ብሄራዊ የትምህርት ቤት ማህበራዊ ሠራተኛ (Social Work) ሣምንት - የ2022 ገጽታ (theme) የሆነው “Time to Shine” የሚል ነው። የአሜሪካ የትምህርት ቤት ማህበራዊ ሠራተኛ (Social Worker) ማኅበር (The School Social Work Association of America (SSWAA)፤ እንዴት የትምህርት ቤት ማህበራዊ ሠራተኞች (social workers) ለተማሪዎች፣ ቤተሰቦች እና የትምህርት ቤት ማህበረሰቦች - አንፀባራቂ-ብርሃኖች እንደሆኑ የሚያከብረውን ገጽታ (theme) መርጠዋል። በአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ውስጥ የሚገኙ ማህበራዊ ሠራተኞች (Social workers)፤ ለሁሉም ተማሪዎቻችን፤ በቅድሚያ-ችግሮችን መለየት፣ መከላከል፣ ጣልቃ-ገብነት፣ ማማከር እና የቀለም ትምህርት ስኬት እንዲኖር እርዳታ መስጠቱን፤ እንዲሁም የትምህርት ፍትሃዊ እኩልነት መገኘቱን ለማረጋገጥ የሚሰሩ ናቸው። ለሁሉም የመማር ዕድልን እንዲያገኙ የሚችሉበትን ሁኔታ ለማሳደግ እንዲረዳ - የማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ እንቅፋቶችን ለመቀነስ ወይም ለማስወገድ ጠንክረው - ከትምህርት ቤት ተቀጣሪ-ሠራተኞች እና ቤተሰቦች ጋር በትብብር ይሰራሉ።

የትምህርት ቤት ማህበራዊ ሠራተኛ (social worker) - በትምህርታዊ ፖሊሲዎችን በመቅረጽ እና ቀውስን-በጣልቃ-ገብነት ለመፍታት የሚረዱም በመሆናቸው፤ ለቀለም-ትምህርት ቡድኑ እንደ-አንድ አስፈላጊ-አካል የሆኑ ናቸው። በACPS ውስጥ፣ በተለይ ደግሞ በCOVID-19 ወረርሽኝ ወቅት፤ ለተማሪዎች ወሳኝ የአዕምሮ ጤና እርዳታ-ሰጪዎች በመሆን አገልግለዋል። በትምህርት-ገበታ መገኘት (attendance) ላይ እርዳታንም የሚሰጡ ሲሆን፣ በትምህርት አሰጣጣቸው ላይ ሳይታተፉ ለቆዩ ተማሪዎቻችን እና ቤተሰቦቻችንን አግኝቶ-በማነጋገር እና ማንኛውም ሊፈጠሩ የሚችሉ እንቅፋቶችን በማስወገድ ይሠራሉ።

የትምህርት ቤት ማህበራዊ ሠራተኞች (social workers) በተጨማሪም፤ እንደ ምግብ፣ ልብስ፣ እና መኖሪያ-ቤት ባሉ ወሳኝ-ነገሮችን የሚገኙበትን የመረጃ-ምንጮች (resources)ን በማገናኘት፤ ከማህበረሰብ አጋሮች እና ከቤተሰቦች ጋር ይሳተፋሉ። በACPS

ውስጥ፤ የማህበራዊ ሠራተኞች (social workers) ቡድናችን - "የተማሪዎቻችንን ፍላጎቶች ለማሟላት ከሚጠቅሙ ከሌሎች ሁሉን አቀፍ የሆኑ አቀራረቦች ጋር በመሆን፣ ተስፋን፣ መገንዘብን፣ እና አክብሮትን እየሰጡ፣ ለበርካታ ቤተሰቦቻችን የህይወት-መስመር ሆነዋል፣" ብለዋል፣ የተማሪ እርዳታ ቡድኖች ዋና ዳይሬክተር የሆኑት ዶ/ር ደሬል ሳምሰን (Dr. Darrell Sampson)።

ያላቸውን ቁርጠኝነት እና ጠንካራ-ስራ በዚህ ሣምንት እውቅና-በምንሰጥበት ጊዜ፤ ለትምህርት ቤት ማህበራዊ ሠራተኞች (social workers) ያላችሁን አድናቆት በመግለጽ፣ እባካችሁን አጋሩ።

## 'ብሄራዊ የአመጋገብ (National Nutrition) ወር'ን፣ ማክበር: የACPS የፎቶ ጽሁፍ (Photo Essay)



https://vimeo.com/683068606/a1b53b319a

በሚገባ-የአመጋገብ ሁኔታው የተጠበቀላቸው ተማሪዎች፣ ለመማር የበለጠ ዝግጁ መሆናቸውን፤ የብሄራዊ የአመጋገብ (National Nutrition) ወር፣ ከመሃል በልባችን-ውስጥ ሆኖ-የምናምንበት ነው። ይህ በማርች (March) ወር ውስጥ የሚደረግ ዓመታዊ ዘመቻ፤ በ'Academy of Nutrition and Dietetics' የተቀረጸ ሲሆን፣ ግንዛቤ-ያለው የምግብ ምርጫዎችን እንዲያደርጉ፣ እና ልብን-የሚያርስ አበላልን ለማጎልበት እና አካላዊ እንቅስቃሴን ልምድን በዓመቱ-ሙሉ የሚዘቅ አድርጎ ለማከናወን - ሁሉንም ሰው ይጋብዛል። የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)፣ በተመጣጠነ ምግቦች፣ ጤናማ መክሰሶች፣ እና የአመጋገብ ትምህርትን የማግኘት ዕድሎችን በማቅረብ፣ ጤናማ የሆነ አካባቢውን ለተማሪዎች ለማቅረብ ይረዳዋል። ተማሪዎቻችንን በተመጣጠነ አመጋገብ በመጠቀን የሚረዱትን፣ በACPS የትምህርት ቤት አመጋገብ አገልግሎቶች ቢሮ (Office of School Nutrition Services) ውስጥ የሚገኙ ሁሉንም ትጉህ፣ ጠንካራ-ሠራተኞቻችንን ሠላምታ እንሰጣቸዋለን።

## በ'ፊት-መሸፈኛ ማድረግ መመሪያ (Masking Guidance)' ላይ፣ አዲስ ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች (FAQs)



ACPS፤ የ2021-22 የኦንላይን የጤና እና የደህንነት-ጥበቃ መመሪያዎችን፣ በትምህርት ቤቶቻችን፣ ተቋሞቻችን እና አውቶቡሶች ውስጥ - የፊት-መሸፈኛ ከማድረግ መመሪያ ጋር (masking guidance) ጋር ተያይዞ - አዲስ ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች (Frequently Asked Questions (FAQs) ጋር፣ አዲስና-ማሻሻያ (updated) አድርጓል። የፊት-መሸፈኛ ማስኮች (masks)ን በትምህርት ቤት ክፍል ውስጥ ከማድረግ ጋር ግንኙነት ያላቸውን በጣም-በቅርቡ ምላሽ-የተሰጠባቸውን ጥያቄዎች ለማየት፤ በhttps://www.acps.k12.va.us/Page/3740 ላይ ኀብኙ።

## በቅርብ ጊዜ የሚከናወን: የ2022 ፍትሃዊ-እኩልነት ለሁሉም (Equity for All Climate) የዳሰሳ ጥናት




ሁለተኛው ዓመታዊ የአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ፍትሃዊ እኩልነት ለሁሉም (Equity for All Climate) የዳሰሳ-ጥናት፤ አርብ፣ ማርች (March) 11 ቀን 2022፣ የሚያስጀምር፣ እና በኦንላይን ላይ በእንግሊዘኛ፣ በስፓኒሽ፣ በአማርኛ እና በአረብኛ የሚገኝ ይሆናል። የዳሰሳ-ጥናቱ፤ ከ6-12 ክፍል ውስጥ ላሉ የ'ACPS' ተማሪዎች፣ ለሁሉም የ'ACPS' preK-12 ቤተሰቦች እና ለሁሉም የ'ACPS' ሠራተኞች፤ እስከ ኤፕሪል (April) 3 ቀን

2022 - እስከ 11:59 p.m. ድረስ ክፍት-ይሆናል። የዳሰሳ-ጥናቱ፤ በሦስተኛ-ወገን ድርጅት ቁጥጥር የሚደረግበት እና ሁሉም ምላሾች በሚስጥራዊነት የሚያዙ ናቸው።

ከ'Equity for All Climate' የዳሰሳ-ጥናት የተገኙ ውጤቶች፤ አሁን-ያለውን ግብ ዓት የሚያቀርብ እና ለመጪው የትምህርት ዓመት ለትምህርት ቤቶቻችን እና መምሪያዎቻችን ዕቅድ-አወጣጥን ለመጠቆም የሚረዳን ይሆናል። የዳሰሳ-ጥናቱ፤ በትምህርት ቤቱ ክፍል ውስጥ በ'Equity For All' ስልታዊ ዕቅድ (strategic plan) ላይ ቁልፍ የሆነ መለኪያ ነው። በACPS ውስጥ - የእናንተን ድምጽ በ'equity climate' ላይ እባካችሁ አጋሩን፣ እና በማርች (March) 11 ቀን 2022፣ የዳሰሳ-ጥናቱ ሲከፈት ተከታተሉ። ለዝርዝሮች እና አዲስና ማሻሻያዎች (updates)፤ www.acps.k12.va.us/equitysurvey2022ን ጎብኙ።

# የሣምንቱ፤ በተጨማሪነት የምንነግራችሁ ነገሮች:

## የCOVID-19 ስርጭት መጠን: ማርች (March) 3 ቀን 2022




እስከ ሐሙስ - ማርች (March) 3 ቀን 2022 ድረስ በነበረው-መረጃ፤ አጠቃላይ አዲስ የCOVID-19 ታማሚዎች - በየ 100,000 ሰዎች፣ ባለፉት ሰባት ቀናቶች ውስጥ፤ 86.98 ነው። የማህበረሰብ ስርጭት የደረጃ-መጠኑ - ጠንካር ያለ ነው። ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት፤ የአሌክሳንድርያ ከተማ የCOVID-19 ዳሽቦርድ (Dashboard)ን ተመልከቱ።

# የትምህርት ቤት ቦርድ አጀንዳ

በማርች (March) 10 ቀን 2022 የሚደረገው የትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ፣ የCOVID-19 አዲስና ማሻሻያ (update)ን፣ እና ስጦታ ያላቸው (Talented and Gifted (TAG)' ፕሮግራም ላይም፤ አዲስና ማሻሻያ (update)ን ያካተተ ይሆናል። የትምህርት ቤት የቦርድ ስብሰባ አጀንዳዎችን እና ሰነዶችን ለማግኘት፤ Electronic School Boardን ይጎብኙ። ስብሰባዎችን በቀጥታ ለመመልከት እና ለመካፈል እንዴት እንደሚችሉ መረጃዎችን ለማግኘትም፤ በSchool Board meeting web page መጎብኘትም ይችላሉ።

# አሁን-ባለንበት ጊዜ ውስጥ፤ ተማሪዎችን ለመርዳት የሚያግዝ የመረጃ-ምንጮች (Resources)

የACPS፣ የተማሪ አገልግሎቶች (Student Services) እና ፍትሃዊ-እኩልነት መምሪያ፤ በአሁኑ-ጊዜ በዩክሬን (Ukraine) ባለው ሁኔታ ጋር በሚያያዝ ነገሮች ላይ፤ ተማሪዎችን ለመርዳት የቀረቡ አንዳንድ ጥያቄዎችን ተቀብሏል።  በአሁኑ-ጊዜ ያለውን ሁኔታ፣ ለአንዳንድ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች፣ እና ከዚህ ቀደም-የነበረ ቀውሶችን ሊያነሳሳ እንደሚችል - በተለይ ደግሞ በቅርቡ ጦርነትን እና ጥቃትን ሸሽተው የመጡ-ሊሆኑ ለሚችሉ ሰዎችን - የሚረብሽ ሊሆን እንደሚችል እንረዳለን። ACPS፣ ሠራተኞች እና ቤተሰቦች፣ ተማሪዎቻችንን ለመርዳት የሚያስችል የኦንላይን መረጃ - የመረጃ-ምንጮች (resources)ን ያቀርባል።